# ከተመቸንማ!

(ከግህሉ በቀለ - ቶሮንቶ)

ባህል ታሪካችን
ቋንቋ ቀለማችን
እምነት ጥናታችን
ተፈጥሮ ዘራችን
ክብር ኩራታችን
ደግነት ፍቅራችን
ቁርጠኛው ጀብዱችን
ጥንታዊነታችን
ብልህነታችን
አርበኛነታችን
ለየት ማለታችን
        ይሄን ነው የጠሉት
        እነደ ጦር የፈሩት
        ከውስጥም ከውጭ
        ጥቁርና ነጭ፡፡

ጠባብ አድር ባዮች
የሳር ውስጥ ዕባቦች
ጨካኝ ትምክህተኞች
አገር በቀል ጉዶች
አደረጓትኮ፤ ታላቋን ኢትዮጵያ
መታሰሪያ ጎሬ፤ ማልቀሻ ማፈሪያ፡፡

የውጭም ጠላቶች፤ የሚያውቁን ጠንቅቀው
ባሳየነው ጀብዱ፤ በአድዋ በማይጨው
ማየት አይፈልጉም፤ አገራችን አድጋ
ስትኖር ተላቃ፤ ከመለስ መንጋጋ
በዘዴ ስታመልጥ፤ ከውድቀት አደጋ

ከተመቸንማ፤ ባንድ ላይ ከኖርን
ከተስማማንማ፤ ባንድ ላይ ከቆምን
ከተዛዘንማ፤ ይቅር ከተባባልን
        ጉዱ ሊፈላ ነው
        ማፈር ሊመጣ ነው
        ሰማይ ሊደፋ ነው
        መግቢያ ሊጠፋ ነው
        በነአጅሬ ሰፈር፤ በአረመኔዎቹ
        በአምባ ገነኖቹ
        በአጉራሽ ነካሾቹ
        ይሉኝታ ቢሶቹ፡፡

ከተመቸንማ፣ ለእድገት ከሰራን
ከተስማማንማ፣ ለሠላም ከቆምን
ከተዋደድንማ፣ ፍቅርን ካሳየን
ከልመና ወጥተን፣ እረጅ ከሆንን
ረሀብን አባረን፣ ጅምናዚየም ከሄድን
ከሽኩቻ ወጥተን፣ መቻቻል ከለመድን
ሙስናን ገልብጠን፣ ህግን ካስከበርን
በሽታን አክመን፣ ዕድሜን ካስረዝምን
ድንቁርና ጠፍቶ፣ ምሁራን ከሆንን
አፈናን አፍነን፣ ነፃነትን ካወጅን
በፍትሀዊ ምርጫ፣ ፓርላማን ከፈጠርን
ፍርሀትና ጭንቀት፣ ስጋትን ካስወገድን
የሠላምን ፍሬ፣ መቋደስ ከቻልን
የገዛ አገራችን፣ ባለቤት ከሆንን
መሰደዱ ቀርቶ፣ ቱሪስቶች ከሆንን
ጉዱ ሊፈላ ነው
ማፈር ሊመጣ ነው
ሰማይ ሊደፋ ነው
መግቢያ ሊጠፋ ነው
በጠረኞች ሠፈር፣ በባለጡንቾቹ
መንታ ምላሶቹ
በሠላም መርከብ ላይ፣ መሣሪያ ጫኞቹ፡፡

ይፈሩናል፣ ይፈሩናል
ስለሚያውቁ ሃይላችንን
ስለሚያውቁ ሀብታችንን
ማየት የሚፈልጉት ውድቀታችንን ነው
ለአገዛዝ የሚመቸው እንደዚያ ስንሆን ነው፡፡

ተንቀን አንቀርም
ጊዜውን ባናውቅም
መለወጥ አይቀርም፡፡

የፈሩት ይደርሳል
የጠሉት ይወርሳል
አበሻ ይነሳል
ድል በድል ይሆናል
ጨለማ ያከትማል
አገር ይባረካል
ሕዝብም እፎይ ይላል፡፡